ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ Since 1991

# መለዕክተ ኢሰመጉ

አንደኛ አመት ቁጥር ሶስት ጥር 2012 ዓ/ም

## ከፍ ያለ ስም

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር

## ሰዋዊ

< <ወንዶም ወዴት ነው? > >

## ቀለም

ሕዝብ ምን ይላል.......?



# ርእሰ አንቀጽ

**ኢሰመጉ**

# የአገራችን ወቅታዊ ሁኔታ በእጅጉ ያሳስበናል!

ተስፋና ሥጋት ይዞ በ2010 ዓ.ም የመጣው ፖሊቲካዊ ለውጥ እየዋለ ሲያድር ከተስፋው ይልቅ ሥጋቱ እያየለ መምጣቱን እያስተዋልን ነው፡፡ ለአንዱ ችግር ‹መፍትሔ ተገኘለት› ብለን ገና በቅጡ እንኳ እፎይታ ሳናገኝ ከሌላ ጥጋት ሌላ ቀውስ የሚፈጠር መሆኑ የአገራችንን ሁኔታ ‹የእንቧይ ካብ› አድርጎታል፡፡

በተለያዩ ሥፍራዎች የሚፈጠሩትና ለሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች መንሥዔዎች የሆኑት ግጭቶች በዋናነት የሚቀሰቀሱት የብሔር ማንነትን መሠረት ባደረጉ በክልልና በዞን የመደራጀት ጥያቄዎች፣ በክልሎች መካከል በሚነሡ የወሰን ግጭቶች ምክንያት ነው፡፡ መንግሥትም «ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን መብት አለው» ከሚለው ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ ጋር በማይጣረስና ዜጎችን ለሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ተጋላጭ በማያደርግ መልኩ ለጉዳዩ መፍትሔ መፈለግ ይኖርበታል፡፡ ከግጭቶቹ በስተጀርባ ግን በየክልሉ ያሉ፤ ፖሊቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ትርፍ የሚያገኙ፣ ከሥልጣን የተነሡም ሆኑ በሥልጣን ላይ ያሉ ሹሞች መኖራቸውን ከመንግሥት በኩል የሚሰጡ መግለጫዎች ሳይቀሩ ያረጋግጣሉ፡፡

በአገራችን ለቀውስ መንሥዔ የሆኑ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ለመቅረፍ በፌደራል መንግሥት ደረጃ የፖለቲካ ፈቃደኛነቱ ያለ ቢመስልም በክልሎች ደረጃ ግን በተለይም በዞንና በወረዳ ደረጃ ያለው ሁኔታ የተለየ ነው፡፡ ዛሬም ሰዎች በብሔር ማንነታቸው ምክንያት ይገደላሉ፣ የአካል ጉዳት ይደርስባቸዋል፣ ንብረቶቻቸው ይወድሙባቸዋል፣ ለዘመናት ከኖሩበት ቀዬአቸው ይፈናቀላሉ፡፡ ይሄ ሁሉ ሲደረግ የክልል ባለ ሥልጣናት ጉዳዩ እንደማይመለከታቸው ሁሉ በቸልታ ይመለከታሉ፤ አንዳንዴም የድርጊቱ ቀጥተኛ ተሳታፊዎችና አስፈጻሚዎች ሆነው ይገኛሉ፡፡

የክልል ፖሊስና ልዩ ኃይል ዜጎችን በእኩልነት በማየት ወንጀል የመከላከል ኃላፊነታቸውን ከመወጣት ይልቅ የተሠማሩበት ክልል መጠሪያ የተሠየመበት ብሔር «ልዩ ጥቅም» አስከባሪዎች አድርገው ራሳቸውን በመቁጠር በኀዳጣን ላይ ለሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ሽፋን ይሰጣሉ፡፡ በየሥፍራው የተነሡ ታጣቂ ኃይሎች ለሚፈጽሟቸው የግድያ፣ የዝርፊያና የእገታ ድርጊቶች መባባስ ምክንያቱ በታችኛው የመንግሥት መዋቅር ያለው የዕዝ ሰንሰለት

መላላትና የፖለቲካ ፈቃደኛነት አለመኖር መሆኑን ከተጨባጭ እውነታዎች መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህም ምክንያት ሥርዓት አልበኛነት ነግሷል፡፡ ሕግ አልባነት ተቀባይነት ያለው፤ የተለመደ የሕይወታችን አካል ሆኗል፡፡ በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የሚቀሰቀሱ ኹከቶችም የዚሁ ነጸብራቅ ናቸው፡፡

በመካከላችን የወንድማማችነት መንፈስ ተሸርሽሮ የ«እኛና እነርሱ» አስተሳሰብ በመግነኑ የማይደፈሩ ቅዱሳን ሥፍራዎች የነበሩ የሃይማኖት ተቋማት የፖለቲካ ጥያቄዎችን በማስታከክ በተደጋጋሚ ውድመት ደርሶባቸዋል፡፡ ዜጎች ለብቻቸው ወይም ከሌሎች ጋር በኅብረት በመሆን በይፋ የማምለክ፣ ሃይማኖታዊ ሥርዓታትን እንዳይፈጽሙ፣ እንዳያስተምሩና እንዳይገልጹ ‹በኀበዝ አለቆች› ሲከለከሉ የጸጥታና የአስተዳደር አካላት መብታቸውን ለማስከበር በቂ እርምጃ ሲወስዱ አይታይም፡፡

ዜጎቿ መሠረታዊ በሆኑት የምግብና የመጠለያና እጦት በሚሠቃዩባት ኢትዮጵያ ከሚንቀሳቀሱ ለቁጥር የበዙ የፖሊቲካ ፓርቲዎች በርካቶቹ የአገራችንን ችግሮች የሚቀርፉና ተጨባጭ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ አማራጭ ፖሊሲዎች ያሏቸው ሳይሆኑ መታገያ አጀንዳቸውን በ‹ብሔር ጥያቄ› ላይ ብቻ ያደረጉ መሆናቸው አሁን ለምናያቸው ችግሮች የራሱን አስተዋጽኦ እንዳደረገ እናምናለን፡፡ በበይነ መረብ በአንዳንድ የማኅበራዊ መገናኛ መድረኮችና መደበኛ የብዙኃን መገናኛ አውታሮች የሚሠራጩ ብሔርና ሃይማኖት ላይ የሚያነጣጥሩ አደገኛ መልዕክቶችም ወደ የእርስ በርስ ግጭት እንዳይመሩን ያሠጋናል፡፡

ስለሆነም፣ ለአገር ሕልውና የሚያሠጉ ቀውሶችን የመፍታትና ችግሮች ተከስተው ወደ ቀውስ ደረጃ ከመድረሳቸው በፊት የመፍትሔ እርምጃ የመውሰድ ዋነኛ ኃላፊነት ያለበት መንግሥት የሕግ የበላይነትን የማስከበር ተግባሩን እንዲወጣ እናሳስባለን፡፡ ነገር ግን፣ መንግሥት ይህን ኃላፊነቱን ሲወጣ የዜጎችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በማይጥስ መልኩ መሆን አለበት፡፡

በአሁኑ ሰዓት እንደምናስተውለው በተለያዩ አካባቢዎች በተለይም በምዕራብ ወለጋ የሚከሰቱ ችግሮችን ለመፍታት የሚወሰዱ ሕጋዊ እርምጃዎችን በተመለከተ ከመንግሥት በኩል በቂ መረጃ ለሕዝብ እየቀረበ ባለመሆኑና የመረጃ ልውውጥ እቀባ በመደረጉ በኅብረተሰባችን ውስጥ ውዥንብር እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል፡፡ ስለሆነም፣ የዜጎችን መረጃ የማግኘት መብት ከግምት ውስጥ በማስገባት በአገራችን ስለሚከሰቱ፣ በዜጎች ሕልውና ላይ ተጽእኖ የሚፈጥሩ ጉልሕ ጉዳዮችን በተመለከተ መረጃ በየጊዜው ይፋ መደረግ አለበት፡፡

በመጨረሻም፤ የአገራችንን ሁኔታ አሥጊ ላደረጉ ችግሮች መፍትሔ መፈለግ የሁላችንም ግዴታ በመሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ አባ ገዳዎች፣ የአገር ሽማግሌዎችና የማኅበረሰብ መሪዎች በዚህ ረገድ ኃላፊነታቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡

## መልእክተ ኢሰመጉ

### አሳታሚ
የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ

### የዝግጅት ክፍሉ ባልደረቦች
ብንያም አባተ
ዳን ይርጋ
ሱራፍኤል ግርማ
ጥበቡ ኃይሉ
ገላውዲዮስ ግሩም

### የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ
የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ
ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7
የቤት ቁጥር= 112/37
ስልክ ቁጥር =0118685706
ፖ.ሳ.ቁ =2432
ኢሜል= info@ehrco.org

ሁሉም መብቶች ለሁሉም!

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ)

ኢሰመጉ በአፍሪካ የሕዝቦችና የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የታዛቢነት ቦታ አለው፤ የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ፌዴሬሽን (FIDH) አባል፣ የዓለም ዓቀፍ ፀረ-ስቃይ ድርጅት (OMCT) አባልና የምሥራቅና የአፍሪካ ቀንድ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ሕብረት (DefendDefenders) መሥራች አባልም ነው፡፡

# እ ፍ ታ

## ዜና




### የፕሮፌሰሩ መቀስ የተሰኘ በ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም ሂዎት ዙሪያ የሚያጠነጥን ዘጋቢ ፊልም ተመረቀ።

ገላውዲዮስ ግሩም

በዳማካሴ ፊልም እና ማስታወቂያ ተዘጋጅቶ ለእይታ የቀረበው ይህ ፊልም 1:55 ደቂቃ እርዝማኔ ሲኖረው የፕሮፌሰሩን ከልጅነት እስከ አሁን ድረስ ያለውን ታሪካቸውን ይተርካል።

በፊልሙ ላይ የጓደኞቻቸው ፣የስራ ባልደረቦቻቸው፣ የቀድሞ የ ቅንጅት እና ቀስተደመና ፓርቲ አመራሮች አስተያየቶች የተካተቱበት ሲሆን ስለ ልጅነት ሂዎታቸው፣ በ አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ እና በውጭ ሀገራት ስለነበራቸው የትምህርት ቆይታ እንዲሁም ስለ አሳለፉት የስራ ዘመን እና በተለይ የ ኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤን በመመስረት ለሰብአዊ መብት ያደረጉትን አስተዋጽኦ በጉልህ ያሳያል።

በምርቃት ስነ_ስርአትም ቤተሰቦቻቸው ጓደኞቻቸው እንዲሁም አድናቂዎቻቸው በተገኙበት የእውቅና ሽልማት እና የክብር ካባ ተበርክቶላቸዋል።

ፕሮፌሰር መስፍንም በብሔራዊ ቲያትር በተዘጋጀው ምርቃት በ አካል በመገኘት ለተደረገላቸው ክብር ምስጋና ያቀረቡ ሲሆን <<ከኔ ቀንሳችሁ ለሀገራቸው ክብር ለተጋደሉት ሁሉ እኔንን ክብር ስጡ>> ሲሉ ተናግረዋል።

# <<ወንድምህ ወዴት ነው?>>

# "ሰዋዊ"

በሱራፍኤል ግርማ

የሰው ደም - ሊያውም የገዛ ወንድሙን - በማፍሰስ የመጀመሪያው ወንጀለኛ ቃየን መሆኑን ከክርስቲያናዊው አስተምህሮ እንረዳለን። ከእልፍ ዘመናት በኋላ ዛሬም በፍኖተ ቃየን እየተንዝን የወንድሞቻችንን ደም ማፍሰሳችንን ቀጥለናል።

የካቶሊካውያን ሊቀ ጳጳሳት ፍራንሲስ እ.ኤ.አ ጥር 1 ቀን 2014 ዓ.ም በተከበረው የዓለም የሰላም ቀን ባስተላፉት መልዕክት የወንድማማችነት መንፈስ ሳይኖር ፍትሕ የሰፈነበት ማኅበረሰብ ለመገንባት እንዲሁም ዘላቂ ሰላም ለማስፈን እንደማይቻል አስገንዝበው ነበር።

በእርግጥም ሊቀ ጳጳሱ እንዳሉት የማሰብ፤ የማገናዘብ ጸጋ የተሰጠን ፍጡራን በመሆናችን የወንድማማችነት መንፈስ መሠረታዊ ሰብዓዊ ባሕርይ ነው። በሕይወታችን ውስጥ ግጭቶች መከሰታቸው የማይቀር ጉዳይ ቢሆንም በመካከላችን ልዩነት ሲፈጠር ሁሌም ወንድማማችና እኅትማማች መሆናችንን ማስታወስና ኀሊቤቶቻችንን ከምድሊ ገድ መጥፋት እንዳለባቸው ጠላቶች ካለመመልከት ራሳችንን ማስተማር ይገባናል። ወንድማማችነት በነጻነትና በፍትሕ፣ በግለሰብ ጥቅምና በማኅበረሰባዊ የጋራ ጥቅም መካከል ሚዛን ስለሚፈጥር ማኅበራዊ ሰላም እንዲሰፍንም ምክንያት ይሆናል።

ይህን እውን ለማድረግ ይቻል ዘንድ ፖለቲከኞች ግልጽና የኀላፊነት መንፈስ በሚንጸባረቅበት መንገድ መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል። ብዙ ጊዜ እንደሚስተዋለው ግን የወንድማማችነት መንፈስን አጥፍተው ግጭት የሚያባብሱ፣ በሌሎች ኪሳራ የአንድ ወገንን ጥቅም ለማስከበር የሚያገለግሉ ፖለቲካዊና ተቋማዊ ሽብልቆች በዜጎች መካከል ይቀረቀራሉ።

በአንድ ወቅት <<ነጻነት፣ እኩልነት፣ ወንድማማችነት>> ጥልቅ የክብር ስሜት የሚፈጥሩ ቃላት ነበሩ። ሰው በሰብዓዊ ፍጡርነቱ ሳይሆን በአመዛኙ በዘሩ፣ በሚናገረው ቋንቋና ከሃይማኖቱ አንጻር በሚታይበት በዚህ ዘመን ግን ዕሤቤዎቹ በፈለቁባት ፈረንሳይ ጨምሮ በሌሎቹ <<ሥልጡን>> አገራት እንኳ ሳይቀር የቃላቱ ትርጉም እየደበዘዘ መምጣቱን ታዛቢዎች ይጠቁማሉ። <<ቴሉ ኖቫ>> የተባለ ግራ ዘመም የሐሳብ ቋት (ቲንክ ታንክ) አባል የሆነው ማርክ ፓዲለ <<ቃላቱ ተመሳሳይ ናቸው፤ የሚሰጡት ትርጉም ግን ተለውጧል።>> በማለት ልዩነቱን ይገልጻል።

በሲዳኒ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ንድፈ ሐሳብና ሥነ መንግሥት ተመራማሪ የሆኑትው ኬቢ ቴይለር ሦስቱ ቃላት በአንድነት ሳይነጣጠሉ መገለጽ ከጀመሩበት የፈረንሳይ አብዮት በመነሣት ባቀረቡትው ትንታኔ ነጻነትና እኩልነት የሚጠናከሩትና <<በተዋኅዶ የሚከብሩት>> በሦስተኛው መርሕ - በወንድማማችነት መንፈስ መሆኑን ታስረዳለች። በኬቢ ገለጻ መሠረት <ነጻነት> ከመንግሥት እርምጃዎች፣ <እኩልነት> ከሕግጋት አተገባበር ጋር የሚገናኙ ሲሆን የወንድማማችነት መሠረቱ ግን ኅብረተሰብ ነው። በፖለቲካዊ የለውጥ ኂደት ውስጥ በምትገኘው ኢትዮጵያ የወንድማማችነት መርሕ መሠረት የሆነው ማኅበራዊ መስተጋብር በቀውስ ውስጥ ይገኛል።

ሁሉን አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ በመጀመሪያው አንቀጹ <<ሰዎች ሁሉ እኩል ክብርና መብቶች ያዘው ነጻ ሆነው ተፈጥረዋል። የማሰብና የማመዛዘን ችሎታ በተፈጥሮ ስለታደሉ እርስ በርሳቸው በወንድማማችነት መንፈስ ሊተያዩ ይገባል።>> በማለት ቢደነግግም የብዝኃነት ሐገር በሆነችው ኢትዮጵያ ግን በአሁኑ ሰዓት እየገነነ ከመጣው ብሔር ተኮር ፖለቲካ አንፃር የወንድማማችነት መርሕ ሲሸረሸር እየታዘብን ነው። የፖለቲካ ቀውስ አትራፊዎች በሚቀሰቅሷቸው ግጭቶች ምክንያት የሚፈጸሙ ድርጊቶች ከወንድማማችነት መንፈስ የሚጻረሩ ናቸው።

በአንድ የአገሪቱን አካባቢ የሚደርስ የተፈጥሮም ሆነ ሰው አመጣሽ ችግር የሁሉም ኢትዮጵያውያን ችግር መሆኑ ታምኖ የተጎዱ ወገኖችን ለመታደግ ሁሉን አቀፍ ርብርብ ይደረግ እንደነበር ዛሬ ግን ዜጎች በሰብዓዊ ፍጡርነታቸው ሳይሆን በነገዳቸውና በሃይማኖታቸው ተመንዝረው የሚታዩበት ጊዜ ላይ በመድረሳችን <<እነርሱ/ሌሎች>> ብለን የፈረጅናቸው ወገኖቻችን ጉዳት ግድ የማይሰጠን ሆኗል።

የጥንቱን ትተን ከቅርብ ጊዜ ታሪካችን እንኳ ለመረዳት እንደምንችለው ኢትዮጵያውያን አገራቸውን የሚወርር የውጭ ጠላት ሲመጣባቸው የውስጥ ልዩነቶቻቸውን በይደር አቆይተው በወንድማማችነት መንፈስ አብረው በመሰለፍ ይመክቱ ነበር። ዛሬስ? በሌላ ሐገር ጦርነት ሳይታወጅብን፤ ነገር ግን እርስ በርሳችን ሰላም አጥተን የገዛ ወንድም እኅቶቻችንን <<ውጡልን ከክልላችን!>> በማለት ባፈናቀልናቸው ዜጎች ብዛት በዓለም ከፍተኛውን ደረጃ ይዘናል። ከማፈናቀል ድርጊቱ በተጨማሪ የተወሰኑ ክልሎችን በሚያስተዳድሩ የፖለቲካ ድርጅቶችና መሪዎች መካከል በተፈጠሩ ልዩነቶች ምክንያት ኢትዮጵያውያን በገዛ ሐገራቸው ከአንዱ <<ክልል>> ወደ ሌላ በነጻነት ለመንቀሳቀስ አለመቻላቸውና በጦርነት ላይ እንደሚገኙ የተለያዩ አገራት ዜጎች የጎሪጥ መተያየታቸው በእጅጉ ያሳዝናል።

በኢትዮጵያዊነት፤ ከፍ ሲልም በጅምላው በሰብዓዊ ወንድማማችነት መንፈስ መተያየትን የሸረሸረው ዜጎችን በጠባቡ የክልል መዋቅር መገደብ ዋና ዓላማው በቋንቋ ላይ የተመሠረቱ ቡድኖች <<ልዩ ጥቅሞችን ማስከበር>> መሆኑን እየተመለከትን ነው። በአብዛኛው ግጭቶች በተፈጠሩባቸውና <<የግጭት ቀጠና ሊሆኑ ይችላሉ>> ተብለው በሚያሠጉ የአገሪቱን ክፍሎች የሚኖሩ ዜጎች በቋንቋ ላይ ብቻ የሚያጠነጥን ፖለቲካ የሚያራምዱ ፖለቲከኞች ሊያሳምኑን እንደሚሞክሩት ከሌሎች ወገኖቻቸው ልዩ የሆኑና አብሮ ለመኖር የሚያበቃ መሠረት የሌላቸው ሳይሆኑ የእርስ በእርስ መስተጋብሩና ሌላው ሁሉ ቢቀር ማንም ሊክደው በማይችለው መልኩ ከአንድ ወንዝ የሚጠጡ ወንድማማች ናቸው።

በአሁኑ ሰዓት ለግጭትና ለሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ምክንያቶች ከሆኑ ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል በተለያዩ ሥፍራዎች የሚቀርቡ በክልል፣ በዞን፣ በልዩ ወረዳ ወዘተ. የመደራጀት እንዲሁም የማንነት ጥያቄዎች ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህ ጥያቄዎች የሚቀርቡበትና ምላሽ የሚያገኙበት አግባብ የኅብረተሰቡን ሰላም አናግቶ አብሮ ለመኖር እንዳይቻል የሚያደርግ መሆን የለበትም። በመሠረቱ፣ የፖለቲካ ፈቃደኛነቱ ካለ ዜጎች አብረው እየኖሩ ቋንቋዎቻቸውን፣ ባሕሎቻቸውን፣ ሃይማኖቶቻቸውን ወዘተ. ማበልጸግ፣ በሌሎች እንዲታወቁና እንዲከበሩ ማድረግ የሚችሉበትን ማዕቀፍ መፍጠር አገር በሚያተራምስ ደረጃ ከባድ ጉዳይ አልነበረም።

ቃየን ለፈጣሪው <<የወንድሜ ጠባቂው እኔ ነኝን?>> እንዳለው ሳይሆን ወደድንም ጠላንም ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ዕጣ ፈንታችን ካይነጣጠል የተጋመደ በመሆኑ በርግጥም የወንድሞቻችን ጠባቂዎች እኛው ነንና በወንድማማችነት መንፈስ አብሮ የመኖር ዕሤታችንን ለማዳስ በግለሰቦች መካከል፣ በፖለቲከኞች መካከል እንዲሁም በማኅበረሰብ ደረጃ በሰከነ መንፈስ ውይይት ማድረግ ይገባናል።

ይህ ጽሑፍ የጸሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።

ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ ሴቶችን በማገልገል!

More than two decades in serving women!

# የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር

ገካካውዲዮስ ግሩም

በሀገራችን ለሰዎች መብት እምብዛም ተደራጅቶ መሟገት ባልተለመደባቸው በነዚያ አመታት፣ በኒያ ሰብአዊ መብት ውስጣችን ዘልቆ ሳይደርስ ለነፃነት ድክድክ ባልንባቸው ዘመናት በተለይ ደግሞ ባህል እና ልምድ ጨምድዶ ይዞን አይደለም ስለሰዎች ስለራሳችን በማንጮህበት ወቅት ሰዎች ሁሉ እኩል መብት አላቸው ብለው ጥቂት ሴቶች ሁሉም ፆታ እኩል ተከብረው እሚኖሩባትን ሀገር አሻግረው ተመለከቱ። ለማንቃት፣ ለመሟገት፣ ለመደገፍ ወገባቸውን ታጥቀው ስራ ጀመሩ።

እንዳለመታደል ሆኖ በሀገራችን ለሀገር ውለታ የዋሉ ግለሰቦችም ይሁኑ ተቋማትን ማመስገን አለመድንም እንጂ በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ 1995 ለሴቶች ደጀን ለመሆን የተነሳው የኢትዮጵያ ህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር ለዚህ አመታትን ለተሻገረ አገልግሎቱ ሊመሰገን በተገባ ነበር።

የኢትዮጵያ ሕግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር (EWLA) ሴቶች ከወንዶች እኩል የሆኑባትን ሀገር ለማየት ራዕይ ሰንቆ በኢትዮጵያ የህግ ባለሙያ ሴቶች የተቋቋመ ትርፋማ ያልሆነ ማህበር ነው ፡፡ ሥራውን የጀመረው እ.ኤ.አ በ 1995 ሲሆን በ 1996 እንዲሁም በተሻሻለው የበጎ አድራጎት እና ማህበራት አዋጅ በድጋሜ በ 2002 እንደ በጎ አድራጎት ድርጅት ተመዝግቧል።

የሴቶች ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊ ፣ ማኅበራዊ እና የህግ መብቶችን ማስፋፋት አላማየ ነው ብሎ እየሠራ ሲሆን ለዚህም በፌዴራል ሕገመንግስት እና በሌሎች ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች ስር የሴቶችን መብት ሙሉ በሙሉ ለማስጠበቅ ይጥራል፡፡

ታዲያ ማህበሩ ተልእኮውን ለማሳካት ሦስት ዋና ዋና መርሃግብሮችን ተግባራዊ አድርጎ ላለፉት 25 ዓመታት ሲሠራ የቆየ ሲሆን በዚህም ለሴቶች እና ለልጆች ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት (አቅርቦት) ፣ የማህበረሰብ ትምህርት እና አቅም ግንባታ እንዲሁም የምርምር እና የህግ ማሻሻያዎች ላይ ለውጥ ለማምጣት ስራዎችን ይሰራል ።

<<ኢውላ>> ከዋና መሥሪያ ቤቱ አዲስ አበባ በተጨማሪ በአዳማ ፣ ናዝሬት ፣ አሶሳ ፣ ባህርዳር ፣ ድሬዳዋ ፣ በጋምቤላ እና በ ሐዋሳ ስድስት ቅርንጫፎች አሉት ፡፡ እነህ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ከታች ጀምሮ በየአቅጣጫው ያሉ ሴቶችን ለመድረስ የሚያስችል ማዕቀፍ በመስጠት በወረዳና በዞን ተደራጅተው 53 የሰለጠኑ የበጎ ፈቃድ ኮሚቴዎች ይደገፋሉ ፡፡

# ከፍ ያለ ስም

እ.ኤ.አ.በ 1996 እውቅና ካገኘበት ጊዜ ጀምሮ በሶስቱ መሪ መርሃግብሮች አማካይነት የፆታ እኩልነትን ፣ የሴቶች ማበረታቻ፣ ሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች እንዲሁም በሌሎች ሴቶችን እሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በስፋት እየሰራ ይገኛል።

የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ ላይም በማተኮር የፆታ እኩልነትን ለማምጣት ጉዳት ለደረሰባቸው ሴቶች ፍትህ እንዲያገኙ ረድቷል።

እስከ አሁን ድረስ ከ 250,000 በላይ ሴቶች እና ሕፃናት ኢውላ በሚሰጠው የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ፍትህን አግኝተዋል።ከዚህም ባለፈ በህግ ማሻሻያ መርሀግብሩ በቤተሰብ ሕግ ፣ በጡረታ ሕግ እና በወንጀል ሕጉ ላይ የሕግ ማሻሻያዎች እንዲደረጉ ጥናቶችን በማጥናት እና በመሟገት የራሱን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከቱ የ ማህበሩ ስኬቶች ተብለው በጉልህ ይጠቀሳሉ፡፡

ሰፊ የሕዝብ ትምህርት ሥራዎች እና ግንዛቤን ለማሳደግ የሚረዱ የድጋፍ ስልቶች በመጠቀም ከ 80,000 በላይ ሰዎች በግንዛቤ ማስጨበጫ እና በአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ተጠቃሚ አድርጓል። በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም ከ 5 ሚሊዮን በላይ ሰዎች በግንዛቤ ፈጠራ ሚዲያ ፕሮግራሞች ለመድረስ ችሏል ፡፡

ይሁን እንጂ ማህበሩ ያለፈባቸው መንገዶች ለዚህ ሁሉ ስኬት ምቹ ሆኖ ሳይሆን አስቸጋሪ እና ዛሬ ላይ ሆነው ሲታዩ የጥንካሬያቸው ምክንያት ምንድነው ብሎ ለመጠየቅ ያስገድዳል። እኛም ለዚህ ጥንቅር በአሁኑ ሰዓት ማህበሩን በ ስራ አስፈጻሚ ዳይሬክተርነት እያገለገሉ የሚገኙትን ሌንሳ በየናን ባነጋገርንበት ወቅት የ ኢውላ የስኬት ሚስጥር ምንድነው የሚል ጥያቄ አንስተን የነበረ ሲሆን እርሳቸውም << የማህበሩ የስኬት ሚስጥር ኢውላ የተቋቋመበት አላማ እና ለተቋቋመበት አላማ የማይደክሙ ቆራጥ ሰራተኞቹ እና በጎ ፈቃደኞቹ ናቸው።>> ሲሉ መልሰውልናል።

መለስ ብለን ስንመለከት በሀገራችን በተለይ የ ሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ላይ ሲወጡ የነበሩ አፋኝ ህጎች ክፉኛ ከጎዳቸው ነገር ግን በዚያ አስቸጋሪ ወቅት ብዙዎቹ ተቋማት ዘዎር ሲሉ የተቋቋሙበትን አላማ ሳይለቁ ታግለው ከቀጠሉ ተቋማት አንዱ ነው።

ዳይሬክተሯ እንዳሉት ታዲያ የማህበሩ የስኬት ሚስጥሮች የሆኑት በጎፈቃደኞች ያለምንም ከፍያ ሰራተኞች ደግሞ ደሞዛቸውን እየዘለሉ ቀላል ከሆኑ የህግ ምክር ድጋፎች ጀምሮ ከፍተኛ የፍርድ ቤት ጉዳዮችን እስከ ሰበር ድረስ ጥብቅና በመቆም አቅመ ደካማ ለሆኑ ሴቶች ፍትሕን እንካችሁ ብለዋል።

ኢውላ ሴቶችን ማእከል አድርጎ ይነሳ እንጂ በርካታ ለሆኑ ትዳሮች አለመበተን እና ለ ህፃናት ያለ እናት ወይንም ያለ አባት አለማደግ ብሎም ጎዳና አለመውጣት የራሱን ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛል።

ለሴቶች ከሚሰጠው የህግ ድጋፍ በተጨማሪም በ አካል እና በኑሮ ለተጎዱ ሴቶች እና ህፃናት ከሌሎች አጋር ድርጅቶቹ ጋር በመተባበር መሰረታዊ የሆኑ የምግብ እና መጠለያ እንዲሁም ህክምና ድጋፎችን ያደርጋል።

በአሁኑ ሰዓትም የተሻሻለውን የሲቪል ማህበረሰብ አዋጅ እና በሀገራችን ላይ የተፈጠረውን መልካም እድል በመጠቀም ከአሁን በፊት ሲሰጥ ከነበረው የሰብአዊ መብት ድጋፍ በበለጠ በ ሙሉ ሀይሉ ሴቶች እኩል መብታቸው ተከብሮ እሚኖሩባትን ሀገር ለመገንባት የበኩሉን ለማበርከት በከፍተኛ መነቃቃት ላይ ይገኛል።

እኛም ቢሯቸው ጎራ ባልንበት ጊዜ በርካታ ፍትህ ፈላጊ ሴቶች፣ እናቶች፣ ልጆች እንዲሁም ወንዶችን ተመልክተናል።

በመሆኑም የኢትዮጵያ ህግ_ባለሙያ ሴቶች ማህበር ሀገር በቀል ሆኖ ለሴቶች እና ሰብአዊ መብቶች በመሟገት ፈር ቀዳጅ በመሆን በ ከባድ ወቅቶች እንኳ ባለው አቅም ማህበረሰቡን በማገልገሉ እያመሰገንን ሀተታችንን በ ዳይሬክተሯ ንግግር እንዝጋ▯▯ ኢውላ በአባላቱ ነፍስ ውስጥ ያለ ከጥቅም እና ከ ስራ በዘለለ ለውስጥ እርካታ የምናገለግልበት ማህበር ነው▯▯

ቸር እንሰንብት▯

ይህ ጽሑፍ የጸሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።

# ኬ ላ

## ሕግ

# የመረጃ እቀባ በኢትዮጵያ (Internet Shutdown)

በዳን ዖርጋ




በዩና ሜሪብ

በይነ መረብ ማለት ሰዎች የኢንተርኔት ቴክኖሎጂን በመጠቀም እርስ በርስ የሚገናኙበትና ሀሳብ የሚለዋመድረክ ነው ሰዎችም ይህንን መንገድ የመጠቀም መብት አላቸው፡፡ ይህ መብት በዚህ በ21ው ክፍለ ዘመን ማለትምየሰው ልጆች የቀን ተቀን የህይወት እንቅስቃሴ ሁሉ በበይነ መረብ አማካኝነት በቴክኖሎጂ የተደገፈ ሆኖዋል በተለይም በበይነ መረብ አማካኝነት ዓለም ወደ አንድ መንደርነት ተቀይራለች በመሆኑም የሰው ልጆችን ሕይወት ከበይነ መረብ ነጥሎ ማየት የሚከብድበት ወቅት ላይ እንገኛለን፡፡

የበዖነ መረብ መብቶች

እነዚህ የበይነ መረብ መብቶች ከጥቂት አመታት በፊት እንደ ቅንጦት መቆጠር ብቻ ሳይሆን እንደ መብትም አይታዩም

ነበር፡፡ የዚህ መብት አንኳር መገለጫዎች ውስጥ የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው

1. ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት፣

2. መረጃ የማግኘት መብት፣

3. መረጃ የመያዝ መብት፣

4. መረጃ የማሰራጨት መብት በዋናነት ይገኙበታል

## ለዕቀባው በመንግስት የሚሰጡ ምክንያቶች

የኢትዮጵያ መንግስት በአብዛኛው ጊዜ የበይነ መረብን ለማቀብ የሚሰጠው ምክንያት ሰላምና ፀጥታን ለመቆጣጠር፣

የፈተና ስርቆትን ለመከላከል፣ በሀገሪቱ የገንዘብና የደህንነት ተጸቋማት ላይ የሚሰነዘሩ የበይነ መረብ ጥቃቶችን

ለመከላከል የሚሉ ምክንያቶች ይገኙበታል፡፡ በነዚህ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች መንግስት በተለያዩ ጊዜያት በበርካታ

የሀገሪ

## የቅርብ ግዜ የበይነ መረብ እቀባ በኢትዮጵያ

ታህሳስ 26 2012 ዓ.ም መንግስት የበይነ መረብ ግንኙነትን ዘግቶ ነበር ለዚህም መንግስት የሰጠው ምላሽ የሀገሪቷን

የገንዘብ ተቋማትላ የተቃጣውን የበይነ መረብ ጥቃት ለመከላከል ነው የሚል መልስ ነበር መንግስት የሰጠው፡፡

በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ወለጋ በሚገኙ ወረዳዎች ውስጥ መንግስት የበይነ መረብ ግንኙነትን ከጥር 23 2012

ዓ.ም ጀምሮ ይህ ፅሁፍ እስከሚዘጋጅበት ጊዜ

ድረስ እንደተቋረጠ ይገኛል፡፡ በተለይም ምዕራብ ወለጋ ሆሮ ጉድሩ ዞን፣

ቄለም ወለጋ፣ ደምቢ ዶሎ፣ ነጆ፣ ጊዳ፣ ቤጊ እና ሌሎችም አካባቢዎች የበይነ መረብ ግንኙነት ተቋርጧል፡፡ በዚህ

አካባቢ ለበይነ መረብ መቋረጥ መንግስት የሰጠው ምላሻ በአካባቢው ያለውን የፀጥታ ሁኔታ ለመቆጣጠርና ሰላምን

ለማምጣት ነው የሚል ነው፡፡

## የበይነ መረብ እቀባ የሚያመጣው የመዋለ ንዋይ ጉዳት

ኢትዮጵያ የበይነ መረብ እቀባ ባደረገች ቁጥር 4.5 ሚሊዮን ዶላር በቀን እንደምታጣ በሪፖርቱ አካቷል 1 ይህም ምን

ያህል ዋጋ እያስከፈለ እንደሚገኝ ከዚህ ሪፖርት በግልፅ ለመረዳት ይቻላል፡፡

እንዲሁም የዜጎችን መረጃ የማግኘትና ሀሳብን የመግለፅ መብት ይገድባል ስለሆነም መንግስት በበይነ መረብ ላይ

የሚያደርገውን እቀባ በጥንቃቄ፣ ግልፅነት በተሞላበት መልኩ ማሰብ ይኖርበታል እላለሁኝ፡፡

ይህ ጽሑፍ የጸሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።

# ቀለም

# ሕዝብ ምን ይላል.......?

ጥበቡ ጎ.

ኢሰመጉ መጪውን ሐገራዊ ምርጫ አስመለክቶ ‹ህዝብ ምን ይላል?› ሲል አጭር የበይነ መረብ ዳሰሳ አድርጎ ነበር፡፡ ዳሰሳው በሁሉም የኢሰመጉ የማህበራዊ ትስስር ገጾች ላይ ተሰራጭቶ የነበረ ሲሆን፤ በቆይታው በአጠቃላይ 62 ያህል ሰዎች የተቀመጡትን 7 ያህል ጥያቄዎች ሙሉ በሙሉ መልስ ሰጥተዋል፡፡ እኛም በዚህ ወር የመልእክተ-ኢሰመጉ እትማችን ይህን የበይነ መረብ ዳሰሳ ውጤት ጥንቀር እንደሚከተለው አዘጋጅተነዋል፡፡

በእያንዳድንዱ ጥያቄዎች ስር ደግሞ የዳሰሳውን ውጤት መሰረት በማድረግ የሚመለከተው አካል ትኩረት ሰጥቶ ቢሰራባቸው የሚባሉትን ነገሮች አስመልክተን ምክረ-ሀሳብ ለማቅረብ እንሞክራለን፡፡

መልካም ጊዜ!

የመጀመሪያው ጥያቄ የነበረው “ወቅታዊውን የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ምን ያህል ይከታተላሉ?” በሚል የቀረበው ጥቅል ጥያቄ ሲሆን፤ “በደንብ እከታተላለሁ”፣ “አልፎ አልፎ እከታተላለሁ”፣ እና “አልከታተልም” የሚሉ የምላሽ አማራጮችን የያዘ ነው፡፡ ይህ ጥያቄ በዋናነት ያስፈለገበት ምክንያት በአጠቃላይ በዳሰሳው የተቀመጡትን ጥያቄዎች ‹ምን ያህሉ መላሾች በመረጃ እና በእውቀት ተመስረተው መልሰዋል› የሚለውን ግምት ለመያዝ እንዲረዳን በማሰብ ነው፡ ፡ በዚህም መሰረት ከአጠቃላይ መላሾች ውስጥ 54ቱ፣

ማለትም 87.1% ያህሉ “በደንብ እከታተላለሁ” የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ቀሪዎቹ 12.9% የሚሆኑት ደግሞ “አልፎ አልፎ እከታተላለሁ” የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ሁለተኛው “በእርስዎ አስተያየት በመጪው ግንቦት 2012 ዓ.ም መደረግ የሚገባው ብሔራዊ ጠቅላላ ምርጫ በተያዘለት የጊዜ ገደብ ውስጥ ያደርጋል ብለው ያስባሉ?” የሚለው ጥያቄ ነበር። ይህ ጥያቄ ደግሞ ቀደም ባሉት ጊዜያት ምርጫ ቦርድ የምርጫ ጊዜ ሰሌዳውን ይፋ ከማድረጉ አስቀድሞ በስፋት ይነሳ የነበረውን ክርክር አስመልክቶ ህዝብ ምን ያስባል የሚለውን ለማወቅ በማሰብ የተዘጋጀ ነበር። በዚህም 58.06% ያህሉ "አይ አይመስለኝም"፣ 35.48% "አዎ እስባለሁ" እና ቀሪዎቹ 6.45% ያህሉ "በቂ መረጃ የለኝም" የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።

ይህም ከአሁን ቀደም ምርጫ በመደበኛነት የሚካሄድበትን የግንቦት ወር ለዘንድሮው ምርጫ ትክከለኛ ወቅት እንዳልሆነ የሚያስረዳ ድምጽ ነው ማለት ይቻላል። መላሾች ከምን ተነስተው ምረጫው ይካሄዳል ወይስ አይካሄድም በማለት ምላሽ እንደሰጡ ለመረዳት የሚያስችሉ ጥያቄዎች ደግሞ በተከታይነት የቀረቡ በመሆኑ እነሱን ለማየት እንሞክር።

ምርጫውን በዋናነት የሚመራው የምርጫ አስፈጻሚ አካል ቁመና ለምርጫው መደረግ ወሳኝ ከሚባሉት ቅድመ ሁኔታዎች አንዱ እንደ መሆኑ ሦስተኛው ጥያቄ ትኩረቱን ያደረገው በዚሁ ላይ ነበር። ጥያቄው "የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ምርጫውን በተያዘለት የጊዜ ገደብ ውስጥ ለማስፈጸም የሚያስችል አቅም እና ዝግጁነት አለው ብለው ያስባሉ?" የሚል ሲሆን፤ "አዎ አስባለሁ"፣ "አይ አይመስለኝም " እና "በቂ መረጃ የለኝም" የሚሉ አማራጮች ነበሩት፡፡ “አይ አይመስለኝም” የሚል መልስ ለሚሰጡ መላሾች ደግሞ ይህን ያሉበትን ምክንያታቸውን መግለጽ የሚችሉበት ክፍት የመልስ መስጫ ቦታ የነበረው ጥያቄ ነበር።

በዚህም መሰረት 33 ከመቶ የሚሆኑት መላሾች “አዎ አስባለሁ”፣ 9 ከመቶ የሚሆኑት ደግሞ “በቂ መረጃ የለኝም” የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ቀሪዎቹ 54 ከመቶ ያህሉ

መላሾች ግን ምርጫ ቦርድ አቅም ያለው “አይመስለኝም” ብለዋል፡፡ ለምላሾቻቸው ምክንያት ብለው ያስቀመጡት ደግሞ በአብዛኛው የቦርዱ የዝግጅት (የምርጫ አስፈጻሚ ምልመላ፣ የቁሳቁስ ማሟላት...) ማነስ፣ የአቅም ውስንነት፣ የጊዜ መጣበብ፣ የልምድና የብቃት ማነስ፣ ከፓርቲ (በተለይም ከገዢው ፓርቲ) ተጽዕኖ ስር ነጻ አለመሆን፣ አስፈላጊዎቹን መመሪያዎች አለማዘጋጀት የመሳሰሉትን ጠቅሰው የምርጫ ቦርዱን ዝግጁነት ላይ ጥያቄ እንዲያነሱ ያደረጋቸው መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ከዚህ አንጻር ምርጫ ቦርድ ለምርጫ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች በፍጥነት እና በከፍተኛ ጥንቃቄ ሊያከናውን እንደሚገባ፣ በየጊዜው የሚደርስበትን ደረጃም ለሕዝብ ሊያሳውቅ እንደሚገባ የሚጠቁሙ አስተያየቶች በመሆናቸው ትኩረት እንዲሰጣቸው ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡

አራተኛው የፖለቲካ ፓርቲዎችን በተመለከተ “ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫው ብቁ ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችል በቂ ዝግጅት እያደረጉ ነው ብለው ያስባሉ?” የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ሕዝብ የፓርቲዎቹን ቁመና እንዴት እንደሚመለከት ለማየት፣ እጅግ የበዛው የፓርቲዎች ቁጥር ከፊታችን ለሚደረገው

ምርጫ የሚኖራቸውን ዝግጅት እንዴት አስቸጋሪ እንደሚያደርገው ብሎም ወቅታዊው የሐገሪቱ ሁኔታ ለፓርቲዎቹ ዝግጅት ምን ያህል ተጽዕኖ አድረጎባቸው ይሆን የሚሉትን ለመለየት እንደሚረዳን በማሰብ የተዘጋጀ ነው፡፡

በዚህም መሰረት ፓርቲዎች ለምርጫው ያላቸውን ዝግጅት አስመለክቶ 13 ከመቶ የሚሆኑት “በቂ መረጃ የለኝም” ያሉ ሲሆን፤ 9 ከመቶ የሚሆኑት ደግሞ “በቂ እንደሆነ አስባለሁ” የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከአጠቃላይ መላሾች 77 ከመቶ ያህሉ ግን የፓርቲዎቹ ዝግጅት “በቂ አይደለም” ሲሉ ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡ ለዝግጅታቸው ማነስ ማሳያ ናቸው ብለው የዘረዘሯቸው ደግሞ የፓርቲዎቹ አደረጃጀትና ቁመና ችግር ያለበት መሆኑ፣ አስፈላጊውን የምዝገባ ስርዓት አለሟሟላታቸው (በምዝገባ ሂደት ላይ መሆናቸው)፣ የመሰብሰብና የመደራጀት መብታቸውን የሚፈታተኑ ተግዳሮቶች መብዛት፣ የፓርቲ ፕርግራማቸውን እያስተዋወቁ አለመሆኑ፣ የጠራ የርዕዮተ አለም አለመያዛቸው፣ የረባ የሚዲያና የፊት ለፊት ሙግት እንኳ ለማድረግ አለመሞከራቸው፣ አስፈላጊው አቅም የላቸውም ለማሰባሰብም እየሞከረ አለመሆኑን እና የመሳሰሉትን ይጠቅሳሉ፡፡ ከዚህ አንጻር ፓርቲዎቹ የሚጠብቃቸው በርካታ የቤት ሥራ እንዳለ ልብ ብለው ሊገነዘቡት የሚገባ መሆኑን ዳሰሳው ያሳያል፡፡

አምስተኛው “ምርጫው በተያዘለት የጊዜ ገድብ እንዳይካሄድ እንቅፋት ሊሆን ይችላል ብለው የሚያስቡት ሁኔታ ምንድን ነው?” የሚለው ሲሆን፤ ወደ ምርጫው ከመግባታችን በፊት በሕዝብ ዘንድ እንደ ስጋት የሚታዩት ችግሮች ምን ምን እንደሆኑ እና የትኞቹ ችግሮች ላይ ትኩረት ሰጥተን መስራት እንደሚገባን ጥቆማ የሚሰጥ በመሆኑ ሦስት አማራጮችና ተጨማሪ ብለው የሚያስቧቸውን ችግሮች የሚዘረዝሩበት ክፍት ቦታ ጭምር ነበር የተዘጋጀው፡፡

በዚህም መሰረት 83 ከመቶ ያህሉ “የሀገሪቱ ሰላምና ጸጥታ ሁኔታ አሥጊ መሆን”፣ 13 ከመቶዎቹ “የምርጫ ቦርድ አቅም ውስንነት”፣ 3 ከመቶ የሚሆኑት ደግሞ “የፖለቲካ ፓርቲዎች ዝግጅት ማነስ” የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በተጨማሪም ከመንግስት በኩል ፍትህ ያለማስከበር እና ለዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ቁርጠኛ ያለመሆን፣ የገዢው ፓርቲ ጣልቃ ገብነት፣ የጽንፈኛ ብሔርተኛ የማኅበረሰብ አንቂዎች (አክቲቪስት)፣ የወጣቶች መደበኛ ያልሆኑ አደረጃጀቶች፣ የማኅበረሰቡ ንቃተ-ሕሊና የመሳሰሉት እንቅፋት ሊሆኑ እንደሚችሉ ተዘርዝረዋል፡፡

ከዚህ አንጻር የሀገሪቱን ሰላምና ጸጥታ የማስጠበቅ ትልቅ ኃላፊነት በመንግስት ላይ የሚጣል በመሆኑ ትኩረት እንዲሰጥበት ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡

ስድስተኛው ጥያቄ “በቅርቡ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ስላጸደቀው የምርጫ፣ ፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና ሥነ-ምግባር ዐዋጅ ምን ያህል ያውቃሉ?” በሚል አስፈላጊው የመረጃ እና የማስተማር ሥራ እንዲሰራ ለማሳሰብ የሚያስችል ግብዓት የተገኘበት ነው፡፡ በዚህም መሰረት 29 ከመቶ የሚሆኑት “በቂ እውቀት አለኝ” በማለት የመለሱ ሲሆን 62 ከመቶ የሚሆኑት ደግሞ “በብዙሃን መገናኛ ከሰማሁት ውጪ በቂ እውቀት የለኝም” በማለት መልሰዋል፤ ቀሪዎቹ 8 ከመቶ ያህሉ “ምንም እውቀት የለኝም” በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ

አንጻር ምርጫ ቦርድም ሆነ ሌሎች ብዙሃን መገናኛ ድርጅቶች የምርጫ ሕጉን ለብዙዎች ተደራሽ በሚያደርግ መልኩ ተከታታይ ሥራ መስራት እንደሚኖርባቸው ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡

በመጨረሻም በበርካታ ብዙሃን መገናኛ አውታሮች በኩል 80 ያህል የፖለቲካ ፓርቲዎች አዲሱን የምርጫ ዐዋጅ አስመልክቶ ያሰሙትን ቅሬታ በተመለከተ ቅሬታው ተገቢ ነው ብለው ያስባሉ ወይ በሚል በአጭር የማብራሪያ ሳጥን እንዲመልሱ ተደርጎ የተዘጋጀ ጥያቄ ነበር፡፡ በዚህም ከ50 ከመቶ በላይ የሚሆኑት ቅሬታው አይደለም ብለው እንዲሚያስቡ ተናረዋል፡፡ በዋነኛነትም ከድጋፍ ፊርማ ጋር ተያይዞ የሚያቀርቡት ቅሬታ ሀገሪቱ ካላት የሕዝብ ቁጥር አንጻር የተቀመጠው ቁጥር ተገቢ እና ፍትሃዊ መሆኑን በመግለጽ ቅሬታቸው ተገቢ እንዳልሆነ ይከራከራሉ፡፡

በእርግጥ የፓርቲዎቹ ቅሬታ ትኩረት ያደረገባቸው ሌሎች ነጥቦች ቢኖሩም መላሾቹ ግን በአብዛኛው ትኩረት ያደረጉት እና

መልስ የሰጡት የድጋፍ ፊርማውን የተመለከተው ላይ በማድረግ ነው፡፡

ከዚህ ውጪ ቀሪዎቹ 30 ከመቶ የሚሆኑት መላሾች ዐዋጁ ለገዢው ፓርቲ ጥቅም የሚሰጥ መሆኑ፣ በጥድፊያ የተዘጋጀ መሆኑ፣ የፓርቲዎቹም ድምጽና ሀሳብ በሚገባ ሊሰማና ሊካተት የሚገባ መሆኑ፣ የሀገሪቱ ሁኔታ የተቀመጡትን ቅድመ ሁኔታዎች ለማሟላት አስቸጋሪ መሆኑ፣ መደራጀት በራሱ ሰብዓዊ መብት በመሆኑ የቁጥር ገደብ ሊጣልበት ተገቢ ባለመሆኑ ቅሬታቸው ተገቢ ነው የሚሉ መከራከሪያ ነጥቦችም አንስተዋል፡፡

ቀሪዎቹ 20 ከመቶ የሚሆኑት በጉዳዩ ተጨማሪ መረጃ እንደሚፈልጉ እና ቅሬታዎቹ ብዙም እውቀት እንደሌላቸው በመግለጽ

ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡

ይህ ጽሑፍ የጸሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።